





# የአሹራ ቀን ፆም ጥቅም

### بسم الله الرحمن الرحيم

إن الحمد لله نحمده، ونستعينه، ونستغفره، ونعوذ بـــالله من شرور أنفسنا وسيئات أعمالنا، من يهـــده الله؛ فـــلا مضل له، ومن يضلل؛ فلا هادي له. وأشهد أن لا إله إلا الله وحده لا شريك له، وأشهد أن محمداً عبده ورســـوله صلى الله عليه وعلى آله وصحبه وسلم.

ምስጋና ለአላህ ስለተገባው እናመሰግነዋለን በሱም እንረዳለን ምህረትም እንከጅላለን ከነፍሶቻችን ሸሮችና ከወንጀል ሥራዎቻችን በአላህ እንጠበቃለን አላህ ቀጥተኛውን መንገድ የመራው ማንም አያጠመውም የተጣመመን ደግሞ ከአላህ በስተቀር ማንም አይመራውም:: ከአላህ በስተቀር በሐቅ ሊያመልኩት የሚገባው አምላክ የለም አላህ አንድ ነው ሽርክም የለውም ነብዩ መሐመድም የአላህ አገልጋይ እና መልዕክተኛ መሆናቸውን እንመሰክራለን ሰላምና ሰላት በአላህ መልዕክተኛ በቤተሰባቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን

የሙሐረም ወር የአላህ ወር በመባል ይታወቃል ሙሐረም ወር በኢስላም በጣም የተባረከና የተለቀ ወር ነው በሒጅሪያም አቆጣጠር የአመቱ መጀመርያ ወር ሲሆን አላህም ከአራቱ የተከበሩ ወሮች መድቦታል



## ከቁርአንም አንቀፅ :-

قال تعالى: ﴿ إِنَّ عِدَّةَ ٱلشُّهُورِ عِندَ ٱللَّهِ ٱثۡنَا عَشَرَ شَهۡرٗا فِي كِتَٰبِ ٱللَّهِ يَوۡمَ خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ مِنۡهَآ أَرۡبَعَةٌ حُرُمٞۚ ذَٰلِكَ ٱلدِّينُ ٱلۡقَيِّمُۚ فَلَا تَظۡلِمُواْ فِيهِنَّ أَنفُسَكُمۡۚ ... ٣٦ ﴾

**ትርጉም (( የወሮች ቁጥር አላህ ዘንድ በአላህ መፅሐፍ ውስጥ ሰማያትንና ምድርን በፈጠረበት ቀን አሥራ ሁለት ወር ነው ከነሱም አራቱ የተከበሩ ናቸው ይህ ቀጥተኛው ሃይማኖት ነው በሱ ውስጥም ነፍሶቻችሁን አትበድሉ))**
አል ተውባህ 36

**አቡበከር (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንዲህ ብለዋል አሉ (አመት ማለት አሥራ ሁለት ወሮች ናቸው ከነሱም ውስጥ አራቱ የተከበሩ ናቸው ሦሥቱ ተከታታይ ሲሆኑ እነሱም ዙል ቂዒዳ ፣ ዙልሒጃና ሙሐረም ፣ ናቸው አንደኛው በጀማዲና በሽዕባን መካከል ያለው ረጀብ ነው) ብለዋል** ቡኻሪ እንደዘገቡት

ሰሂሄን ሐዲስ ላይ እንደተዘገበው ኢብኑ አባስ ( ረዲየሏሁ አንሁ ) እንዳስተላለፉት ነብዩ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com

(ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም ) ወደ መዲና በመጡ ጊዜ የሁዶች የአሹራን ቀን ሲፆሙ አገኙዋቸው::

ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም ) ይህ የምትፆሙት ቀን ለምንድን ነው ብለው ጠየቋቸው :
የሁዶችም ይህ ቀን የተከበረ ቀን ነው አላህ ሙሳንና ተከታዮቹን አትርፎ ፊርዐውንንና ተከታዮቹን ያሰመጠበት ቀን ስለሆነ አላህን ለማመስገን ነብዩ ሙሳ ስለፆሙት እኛም እንፆመዋለን አሉ ::

በዚህን ጊዜ ረሱል ( ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም ) (እኛ ከናንተ የበለጠ ለሙሳ የቀረብን ነን) ብለው መፆም ጀመሩ ::

በአሁኑ ዘመን ክርስቲያኖች ከነብዩ ኢየሱስ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌላቸው ሁሉ የሁዶችም ከነብዩ ሙሳ ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም ሙስሊሞች የነቢያቶችን ደረጃ አላህ በቁርአን በገለፀው መሠረት ብቻ ስለሚያምኑ ላለፉት ነቢያቶች ሁሉ የቀረቡ ናቸው ::

## የአሹራ ፆም በሦስት አይነት ይከፈላል

**1ኛ** - ሙሐረም አሥር የአሹራ ቀን ብቻ መፆም

**2ኛ** - ሙሐረም ዘጠኝና ሙሐረም አሥርን መፆም ምክንያቱም ኢማም



አህመድ እንደዘገቡት ነብዩ ( ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም ) (መጪው አመት ድረስ ከቆየሁኝ ሙሃረም ዘጠነኛውንና አሥረኛውን ቀን እፆማለሁ ) ብለዋል ::

ይህንን ሃዲስ በመንተራስ አብዛኛው ዑለማዎች ዘጠነኛውን ቀን ከአሹራ ጋር አከታትለው ይፆማሉ ከነሱም ውስጥ ኢማሙ ሻፊዒይና ኢማሙ አህመድ ይገኙበታል ::

**3ኛ** - ሙሐረም ዘጠኝ ሙሐረም አሥር ( የአሹራ ቀን ) እና ሙሐረም አሥራአንድን ሦስት ቀን መፆም ሌላው አይነት አፂፂም ነው ::

በተጨማሪ የፈለገ ሙስሊም የአሹራን ቀንና ሙሐረም አሥራአንድን መፆም ይችላል ምክንያቱም ረሱል ( ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም ) የአሹራን ቀን ፁሙ የሁዶችም ስለሚፆሙት ከነሱ ላለመመሳሰል ጭማሪ አንድ ቀን አስቀድማቹህ ወይንም አስከትላቹህ ፁሙት ) ብለዋል :: « አህመድ እንደዘገቡት »

በየትኛውም መልኩ ይህንን የአሹራ ቀን መፆም ወደ አላህ መቃረብና ነብዩ ሙሳን ( ዐለይሂ ሰላም ) አላህ ከፊርዐውን ጥቃት ስላተረፋቸው ለአላህ ምስጋና ማቅረብ ነውና ሙስሊሞች ይህንን ቀን ቢፆሙት ብዙ ምንዳ ያገኙበታል ::

ኢብኑ ቁዳማ ሙግኒ በሚለው ኪታባቸው ላይ የኢማም አህመድን ቃል ሲያሰፍሩ :-
ኢማም አህመድ (ረሒመሁሏህ ) እንዲህ ብለዋል :- ሰለፎች ሲፆሙ ወደ ውጭ ሳይወጡ መስጊድ ውስጥ ቁጭ ብለው እርስ በርስ እንዳንተማማና ስራችን እንዳይበላሽ ፆማችንን እየጠበቅን ነው ይሉ ነበር ::



ስለዚህ እኛ መስጊድ ውስጥ ቁጭ ብለን ፆማችንን ለመንከባከብ ጊዜ ባናገኝም በተቻለ መጠን በተሰማራንበት ሁሉ ሆዳችን እንደፆመ ምላሳችን መጥፎ ከመናገር አይናችን ሐራም ከማየት ጆሮአችን መጥፎ ከመስማት መቆጠብ አለባቸው ::

ረሱል ( ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ) ( ልቅ ንግግርንና መጥፎ ስራን ሳይተው ምግብን ብቻ ትቶ ለሚፆም ሰው አላህ ጉዳዩ አይደለም) ብለዋል :: « ቡኻሪ »

በመጨረሻ የአሹራንም ሆነ ማንኛ ውንም አይነት ፆም ሲፆም ከመጥፎ ቃልና ተግባር መቆጠብ ግዴታ ነው ከፆም ውጪም ቢሆን በመልካም ሥነ - ምግባር መገኘት የሙስሊም የዘውትር ባህሪው መሆን አለበት ::

ወቢላሂ ተውፊቅ ወሰላም አለይኩም ወራህመቱላሂ ወበረካቱሁ

ትርጉም እና ዝግጅት
ሰይፈዲን ሐበሻ ያሲን

ከጅዳ የዳዕዋ ማዕከል
1927 ዓመተ ሒጅራ

PDF created with pdfFactory Pro trial version www.pdffactory.com